በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ.መ.ቁ 211028

ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ሙሴ ራሕመቶ - ለሁለቱም አመልካቾች ጠበቃ አድነው አቡሼ ቀረቡ

2. አቶ ሀብታሙ አያሌው

ተጠሪ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ - አልቀረበም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 289199 ሰኔ 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 272623 ሐምሌ 05 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው ክሶች ሁለት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- 1ኛ አመልካች የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 131(1)(ለ) በመተላለፍ በአዲስ አበባ ከተማ በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ክልል ልዩ ቦታው በርበሬ በረንዳ እየተባለ በሚጠራው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አካባቢ ከሚገኘው የንግድ ድርጅታቸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝግበው መሳሪያውን አውጥተው ሥራ ላይ ካዋሉ በኋላ በቀን 17/03/2013 ዓ.ም ከቀኑ 5:30 ሰዓት ሲሆን 1ኛ የዐቃቤ ህግ ምስክር 4 የበረንዳ ዣንጥላ የአንዱ ዋጋ ብር 150 በጊዜው የሽያጭ ሰራተኛ ከነበረው ከ2ኛ አመልካች ጋር ተስማምተው የአራቱ ዋጋ ብር 600 ብር ከፍሎት ለተከናወነው ግብይት ከማሽን ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባው ያልተቆረጠ በመሆኑ በፈጸመው ደረሰኝ ሳይቆርጥ ግብይት ማከናወን ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ክስ፡- 2ኛ አመልካች የፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/08 አንቀጽ 131(1)(ሰ) እና 128 በመተላለፍ በውክልና በሚያስተዳድረው በ1ኛ አመልካች ስም በተመዘገበው የንግድ ድርጅት ውስጥ በ1ኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ላይ ለተከናወነው ግብይት ከማሽን የወጣ ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባው ያልቆረጠ በመሆኑ በፈጸመው 1ኛ አመልካች በሕግ የተጣለበትን በደረሰኝ ግብይት ማከናወን ግዴታ እንዳይወጣ ማበረታታት እና መርዳት ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

አመልካቾች ክሱ ተነበባቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ እንደሌላቸው ገልጸው የእምነት ክሕደት ቃላቸውን ሲጠየቁም ድርጊቱን አልፈጸምንም ብለው ከደው በመከራከራቸው ፍርድ ቤቱ የዓቃቤሕግን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ ዓቃቤሕግ ባቀረበው የሰው እና የሰነድ ማስረጃ እንደክሱ አስረድቷል በማለት የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካቾችም ክሱን ለመከላከል ያስችለናል ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ በ1ኛ አመልካች ንግድ ድርጅት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰውን ግብይት ያለደረሰኝ መከናወኑ ተረጋግጧል፤ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2009 አንቀጽ 132/2/ በሚያዘው መሰረት 1ኛ አመልካች የንግድ ድርጅቱ ባለቤት እና ስራ አስኪያጅ እንደመሆኑ መጠን ገንዘብ ተከፍሎ ደረሰኝ ከቀረበ በኋላ ብቻ እቃ ለገዢ እንዲሰጥ የሚያደርግ ቀላል አሰራር ስርዓት እንኳን ስለመዘርጋቱ አላረዳም፤ 2ኛ አመልካችም ግብይቱን እንዳከናወነ እና ገንዘቡን ከመቀበሉ በፊት ደረሰኙን ቆርጦ ማዘጋጀት ሲገባው ይህን ሳያደርግ የዓቃቤሕግ ምስክሮች መጣሁ ብለው ሄዱ ማለቱ ከተጠያቂነት አያድነውም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በዓቃቤሕግ የተረጋገጠባቸውን ፍሬ ነገር ስላላስተባበሉ በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኛ ናቸው በማለት 1ኛ አመልካችን በአንድ ዓመት ፅኑ እስራት፣ 2ኛ አመልካችን ደግሞ በአንድ ዓመት ከ2 ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል የወሰነ ሲሆን አመልካቾች ያቀረቡትን የቅጣት ይገደብልኝ ጥያቄ በሚመለከት ደግሞ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

አመልካቾች ሐምሌ 12 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- 1ኛ አመልካች በግብይቱ

ተሳታፊ አይደለም፤ በ2ኛ አመልካች ላይ ክስ ባልቀረበበት አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 131/1/ለ እና 128 ስር ጥፋተኛ መባሉ አግባብ አይደለም፡ 2ኛ አመልካች የዓቃቤሕግን ምስክሮች ደረሰኝ ውሰዱ እያሉ እየጠሩ እንዳልሰሙ መስሰው እየሮጡ መሄዳቸውን አስረድቷል፤ 2ኛ አመልካች ያቀረቧቸው የቅጣት ማቅለያዎች አላግባብ ውድቅ ተደርገዋል፤ ቅጣቱ እንዲገደብ ያቀረብነው ጥያቄ ውደቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብነት፣ ጥፋተኛ ቢሆኑ እንኳን ቅጣት እንዲገደብ የቀረበው ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ ሕዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- 1ኛ አመልካች በቦታው ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን የመመዘን ስልጣን የሌለው ሲሆን ግብይቱ ሲፈጸም በረንዳ ላይ እንደነበረ ተረጋግጧል፤ በ2ኛ አመልካች ላይ በዋና ወንጀል አድራጊነት በሚል ክስ አልቀረበም፤ 2ኛ አመልካች 1ኛ አመልካች ያሰተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት እንዲፈጽም እንደረዳው ወይም እንዳበረታታው ተረጋግጧል፤ 2ኛ አመልካች በአንድ በኩል በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 131/1/ለ እና 128 ስር ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ እንደተባለ እየተከራከረ በሌላ በኩል በዚሁ ድንጋጌ ክስ ሳይቀርብብኝ ጥፋተኛ ተብያለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፤ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ እንደክሱ አስተድቷል፤ አመልካቾች የገንዘብ መቀጮውን መክፈላቸውን የተጣለባቸውን ቅጣት አያስቀርም፤ አመልካቾች ላይ የተጣለባቸው ቅጣት ወደ ገንዘብ መቀጮ ሊቀየር የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፤ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን ለመገደብ በህጉ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን ካለማሟላታቸው በተጨማሪ ገደቡ አመልካቾችን ሊያስተምራቸው የሚችል ስለመሆኑ ስላልታመነ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው የሚል ነው።

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች 2ኛ አመልካች በውክልና በሚያስተዳድረው በ1ኛ አመልካች ስም በተመዘገበ የንግድ ድርጅት ውስጥ በክሱ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ስለመሆኑ እና ባቀረበው መከላከያ ማስረጃም በዓቃቤሕግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ፍሬነገር ማስተባበል ያልቻለ ስለመሆኑ ተረጋግጧል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለዚህ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን አያጣራም ማስረጃን አየመዝንም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬነገር መሠረት በማድረግ በ2ኛ አመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ ሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት ቅጣት እንዲገደብ የቀረበውን ጥያቄ በሚመለከት ምክንያት ሳይሰጥ ተቀባይነት የለውም በሚል ውደቅ ማድረጉ አግባብ ባይሆንም በወንጀል ሕጉ ላይ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ ቅጣቱን ለማስገደብ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ 2ኛ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመቀጠል 2ኛ አመልካች ድርጅቱን በውክልና ሲያስተዳድር ለፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛ በተባለበት ሁኔታ 1ኛ አመልካች የድርጅቱ ባለቤት ነው ከሚል መነሻ በወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ ሊሆን ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 285/94 በአዋጅ ቁጥር 609/2001 እንደተሻሻለው አንቀጽ 56/1/ አንቀጽ 22/1/ እና አንቀጽ 50/ለ/1 መሠረት የአንድ የንግድ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በወንጀል ተጠያቂ የሚሆነው እሱ የሚመራው ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ሆኖ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማከናወኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ፣ የድርጅቱ ሃላፊነት ከተረጋገጠ የሥራ አስኪያጁ ሃላፊነት የሕግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ እንገነዘባለን፡፡ ሆኖም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱን አስተዳደር በሚመለከት በውክልና ለሌላ ሰው ያስተላለፈ መሆኑ እና ተወካዩም በተቀበለው ውክልና መሠረት ሥራውን የሚያከናውን መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆነው ውክልናውን ተቀብሎ ስራውን በውክልና የሚያስተዳድረው ሰው እንጂ ስራ አስኪያጁ ወይም የድርጅቱ ባለቤት ሊሆን አይገባም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ዓቃቤሕግ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ 2ኛ አመልካች በውክልና በሚያስተዳድረው በ1ኛ አመልካች ስም በተመዘገበ የንግድ ድርጅት ውስጥ ድርጊቱ የተፈጸመ መሆኑን የገለጸ ሲሆን 1ኛ አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2010 ዓ.ም 2ኛ አመልካች የንግድ ቤቱን እንዲያስተዳድርለት የሰጠው ውክልና በዓቃቤሕግ በኩል በማስረጃነት የቀረበ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠቃሹ ድርጅት በ1ኛ አመልካች ስም የተመዘገበ ቢሆንም 1ኛ አመልካች በሰጡት ውክልና መሠረት 2ኛ አመልካች ድርጅቱን የሚያስተዳድር መሆኑ እስከተረጋገጠ ጊዜ ድረስ 1ኛ አመልካች ለተፈጸመው የወንጀል ድርጊት ሀላፊ የሚሆኑበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት 1ኛ አመልካችን ከክሱ በነጻ ማሰናበት ሲገባቸው በ1ኛ አመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሰጥተናል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 289199 ሰኔ 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ፣ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 272623 ሐምሌ 05 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሸሽሏል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች በ1ኛ አመልካች ላይ ያስተላለፉት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ተሽሮ 1ኛ አመልካች ከቀረበበት ክስ በነጻ እንዲሰናበት ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት በ1ኛ አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤቶች ተላልፎ የነበረው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሻረ መሆኑን አቅቶ 1ኛ አመልካችን በሌላ ጉዳይ የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ ከእስር እንዲለቀ ታዟል። በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ማስፈጸም ይቻለው ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው ተብሏል።
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም